የአብክመ ገቢዎች ቢሮ
ANRS Bureau of Revenue
በለምናነትአግልጋይ ደስታ ደስሞናል - Serve with Passion

ቁጥር ገቢዎች-4.1/348
Ref.No
ቀን 6 /10/2018

ለ14ቱ ዞን አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ
ለ8ቱ ሪጅኦፖሊታን ከተማ አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ
ቢያሉበት

ጉዳዩ፡-የቴምብር ቀረጥ ለማሻሻያ የወጣ አዋጅ ስለመላክ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ምክር ቤት 6ኛ ዙር ፣ 5ኛ ዓመት ሥራ ዘመን፣ 11ኛ መደበኛ ጉባኤ የቴምብር ቀረጥ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 307/2018 ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም የቴምብር ቀረጥ አዋጁ ወደ እንግሊዘኛ ተቀይሮ አስከሚታተም የተሻሻለውን አዋጅ 10 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላከን መሆኑን እየገለጽን አዋጁ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንድታደርጉ በጥብቅ አሳስባለሁ፡፡

"ግብር ለሀገር ክብር "

ግልባጭ
- ለደንበኞች አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት
- ለግብር አወ/አሰ/ክት/ዋና የሥራ ሂደት
- ለታክስ አዲትና ህግ ማስከበር ዋና ሥራ ሂደት
- ለግብር ትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዋና የሥራ ሂደት
- ለታክስ ኢንተሊጀንስ ዋና የሥራ ሂደት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት
- ለታክስ ጉዳዮች አማካሪ

ገቢዎች ቢሮ
ባህር ዳር

መንግሥቴ ፈንታው ንጋቱ (ዶ/ር)
Mengesha Fentaw Nigatu (PhD)
ቢሮ ኃላፊ
Bureau Head

TA/EG
D:\Gen.Dir \Letters\memos\Letter2

☎ 058 226 57 76 /058 226 57 74
Fax 058 222 20 71 /058 226 57 80
Email- amhararevenue@ethionet.et
✉ 746

አዋጅ ቁጥር ፫፻፷/፪ሺ፲፰

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴምብር ቀረጥን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሰነዶች ላይ የተጣለው የቴምብር ቀረጥ የኪነጥበብ ዕድገትንና የካፒታል ንብረት ዝውውርን ለማገዝ በሚያስችል አኳሃን እንዲሻሻል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በስራ ላይ ያለው የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር ፴፭ /፭ሺ፱፻፭ የተቀመጠው የቴምብር ቀረጥ ማስከፈያ ምጣኔ ከጀመ ዓመት በላይ ያስቆጠረና በሰነዶች ላይ የሚሰበሰበው የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ዝቅተኛ በመሆኑ ከተገልጋዮች የመክፈል አቅም ጋር የተመጣጠነ አድርጎ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከዚህ በፊት በተለያየ ጊዜ በቴብር ቀረጥ አዋጅ አስመልክቶ ማሻሻያ የተደረገባቸው አዋጆች ለአፈጻጸም እንዲያመች በዚህ ማሻሻያ አዋጅ አጠቃሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፱(፫) እና ፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷/፪ሺ፲፰ "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ :-

፩. "ግልግል" ማለት ስለግልግል፣ ስለእርቅ፣ ስለስምምነት ወይም ስለሌላ ተመሣሣይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍርድ ቤት ሣይሆን በገላጋዮች አልቆ በጽሁፍ የተሰጠ ውሣኔ ነው፡፡

፪. "ማገጃ" ማለት የተወሰነ ነገር በመፈፀሙ ወይም ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጪው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል፡፡

ፎ. "የህብረት ስምምነት" ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሠራተኞች ማህበራት ወኪሎች እና በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ አሰሪዎች ወይም የአሰሪ ማህበራት ወኪሎች ወይም አሰሪዎችን በሚወክሉ ተጠሪዎች መካከል ስለ ስራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጽሁፍ የሰፈረ ስምምነት ነው።

ፏ. "የሥራ ውል" ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪ መሪነት በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ሲስማማ በሁለቱ መካከል የሚሰሩት ውል ነው።

ፐ. "ሰነድ" ማለት ማናቸውም መዛት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት ወይም የተጠቀሰው ግዴታ ተፈጽሟል የተባለበት ማናቸውም የጽሁፍ መረጃ ነው።

ፑ. "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብ ቢሮ ነው።

ፒ. "ገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ሲሆን በየደረጃ ያሉትን የገቢ ተቋማትን ይጨምራል።

ፓ. "ማረጋገጫ" ማለት የህዝብ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ስልጣን ባለው ሰው በሰነዶች ላይ የሚሰጥ ምስክርነት ነው።

ፔ "አካል ጉዳተኛ" ማለት በፌደራል በአዋጅ ቁጥር 568/2000 አንቀጽ ፪ (፩) መሠረት የደረሰበትን የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳት ተከትሎ በሚመጣ የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊ ወይም የባህላዊ መድሎ ሳቢያ በሥራ ስምሪት የእኩል እድል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ነው።

ፍ. " ሰነድ ማስፈጸም" ማለት መስራት፣ ማውጣት በሰነዱ የተመለከተውን ማስፈጸም ወይም ሰነዱን ማዛወር ነው።

፲፩. "የመያዣ ሠነድ" ማለት ተበዳሪው ወይም ዋስ ለአበዳሪው በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበት ሰነድ ነው።

፲፪. "ስታርትፕ" ማለት ምንም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ታሪክ ሳይኖረው ወይም የተወሰነ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ታሪክ ብቻ ኖሮት ኢኖቬሽንን ተግባራዊ የሚያደርግ፣ የቴክኖሎጂ ወይም ቡቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ተመንዳጊ እና የገበያ መዋቅር የሚለውጥ ምርትን፣ አገልግሎትን ወይም ሒደትን በማስተዋወቅ በመፍጠር፣ በማበልጸግ፣ ሽግግርና ማላመድ በማድረግ ወይም በምልስ ምሕንድስና አማክኝነት ኢኮኖሚያዊ ዕሴትን በመፍጠር ላይ የተሰማራ ቡድን ወይም ሰው ነው።

፲፫. "መተዳደሪያ ደንብ" ማለት አንድን ድርጅት ለማቋቋም የተዘጋጀ ደንብ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍ ነው።

፲፬. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማናቸውም ድርጅት ነው።

፫. የቴምብር ቀረጦች የሚከፈልባቸው ሰነዶች

የሚከተሉት ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ ይከፈልባቸዋል።

፩. የማንኛውንም ንግድ ማህበር፣ የህብረት ስራ ማህበር ወይም የማንኛውንም ዓይነት ማህበር መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣

፪. ግልግል

፫. ማኅተም

፬. የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ፣

፭. ውል፣ ስምምነትና የእነዚህ መግለጫ፣

፮. የመያዣ ሰነዶች፣

፯. የሕብረት ስምምነት፣

፰. የሥራ /ቅጥር/ ውል፣

፱. የኪራይ፣ የተከራይ አከራይና መሰል መብት የማስተላለፊያ ሰነዶች ጭምር ፣

፲. ማረጋገጫ ፣

፲፩. የውክልና ሥልጣን፣

፲፪. የንብረት ባለቤትነትን ማስመዝገቢያ ሰነድ፣

፬. የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ልክ

፩. በአንቀጽ ፫ ስር በተመለከተው በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ መክፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ከዚህ ጋር በተያያዘውና የዚህ አዋጅ አንድ አካል ሆኖ በሚቆጠረው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተዘረዘረው ይሆናል።

፪. አንድ ሰነድ ለፀኛ ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው ነው።

፫. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል በአባሪ ሠንጠረዥ ውሥጥ ለተራ ቁጥር 1 (ለ) ለተጠቀሰው ድንጋጌ የገቢዎች ቢሮ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፰. የቀረጡ አተማመን

፩. በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነዱ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል።

፪. በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይችል ከሆነ በዚሁ ሰነዱ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል።

፫. አንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረጥ በብር ላይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጠመበት ቀን በዋለው የምንዛሬ ልክ ነው።

፬. በስቶክ ወይም ሌላ ዋስትና ባለው ነገር ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካይ ዋጋ መሠረት ነው።

፭. ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለለበት ወይም የተካተተበት ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል።

፮. ንብረትን በባለቤትነት ለማስመገዝገብ በተቋቋመ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በገቢዎች ቢሮ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው።

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ የተደነገገው ቢኖርም በንብረቱ ሰነድ ላይ የተመለከተው ዋጋ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ያልተቀበለው እንደሆነ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ ለዚህ ጉዳይ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ የወቅቱን የገበያ ዋጋ አጥንቶ ይወስናል።

፮. የክፍያ ግዴታ

፩. በዚህ አንቀጽ ከዚህ በታች በተመለከቱ ንዑስ አንቀጾች በሌላ አኳሃን ካልተገለጸ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብ ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት፣

፪. በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱ የሚሰራው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ አለበት። ሆኖም አንድ ሰነድ የተሰራው ወይም የተሰጠው ከኢትዮጵያ

ውጪ ከሆነ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰነዱን ኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈጸመው ሰው ነው።

፫. በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኪራይ ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው።

፬. በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ ተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት፣

፭. በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረቱ ባለቤትነት የሚመዘገበው ሰው ነው።

፮. ውል ወይም ስምምነት የሚመሰርቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል።

፯. በትጥር ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሰሪው ነው።

፰. ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው።

፱. በሕብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሰሪውና ሰራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

፮. ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ

፩. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በሚከተለው ጊዜና ሁኔታ ነው።

ሀ. ከመመስረቻና መተዳደሪያ ጽሁፎች ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ፣

ለ. በግልግል ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ፣

ሐ. በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፣

መ. በኪራይ ወይም በተከራይ አከራይ ውል ላይ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፣

ሠ. በማረጋገጫ ሰነድ ላይ ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ፣

ረ. በመያዣ ሰነድ ላይ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፣

ሰ. በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የማስመዝገብ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ፣

፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር ፱ (አንድ መቶ) በታች በሚሆንበት ጊዜ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይሆናል።

፲. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር ፱ (አንድ መቶ) የበለጠ ሊሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሰራርን የሚጠይቅ ከሆነ የገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል።

፲፩. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች ፣

ሀ. የቴምብር ቀረጥ በተለጠፈበት ሰነድ የሚሰራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሰራ መሰረዝ አለበት፣

ለ. ቴምብር የተለጠፈበትን ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሰራረዝ ፣

ሐ. በሰነዱ ላይ የተለጠፈ ቴምብር ካልተሰረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጥራል፣

መ. ሰነዱ ካልተሰረዘ በዚህ ምክንያት የሚመጣው ሃላፊነት የሚወድቀው በባለጉዳዩ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሰጥ ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ነው፣ የገቢዎች ቢሮ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፰ የአማራ ብሔራዊ ክልል ገቢዎች ቢሮ ሥልጣን

፩. በዚ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን ቀረጥ ለመሰብሰብና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም፣

፪. ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ መዛግብትንና ደብተሮችን፣ ወረቀቶችን ማንኛውንም ልዩ ልዩ ሰነዶችንና ውሳኔዎች እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ራሱ ቀርቦ እንዲያከመረምር ወይም እንዲያስረዳ ለማዘዝ፣

፫. ጉዳዩ የሚመለከተው ቀረጥ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሳይሆን በቀረ ጊዜ ቀረጡን በግምት ለመወሰንና ለመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፱. ቅሬታ የማቅረብ መብት

የገቢዎች ቢሮ በወሰነው የቴምብር ቀረጥ መጠን ላይ የማይስማማ ማናቸውም የቴምብር ቀረጥ ከፋይ የገቢዎች ቢሮ ውሳኔውን በጽሁፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ በ ፴፩ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል።

፲. ይግባኝ የማቅረብ መብት

፩. በማንኛውም የቴምብር ቀረጥ አወሳሰን ላይ ገቢዎች ቢሮው በሰጠው የቅሬታ መልስ ካልረካ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ማቅረብ ይችላል፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞች ፦

ሀ) የቴምብር ቀረጥ ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የቴምብር ቀረጥ መጠን ፶ (ሃምሳ) በመቶ ወለድና ቅጣት ሳይጨምር ለገቢዎች ቢሮው ካላስያዘ፣ እና

ለ) የቀረጥ ውሳኔ ማስታወቂያው ወይም በቅሬታ አጣሪ ቡድን የተሰጠው ውሳኔ ለቴምብር ቀረጥ ከፋዩ በደረሰው በ፴ ቀን ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ በይግባኝ ሰሚው ጉባዔው ተቀባይነት አይኖረውም፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) "ሀ" እና "ለ" የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፯፩/፪ሺ፭ ዓ.ም ውስጥ በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ ወይም ይግባኝ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናል።

፲፩. የግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሳኔን በመቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ፣

፩. የግብር ይግባኝ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ስህተት አለው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የግብር ይግባኝ ጉባዔው ውሳኔ በደረሰው በ ፴ ቀናት ውስጥ የአከራካሪውን ፭፩ በመቶ ወለድና ቅጣት ሳይጨምር ለገቢዎች ቢሮ በመክፈል በአካባቢያቸው ወደ ሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።

፪. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሕግ ትርጉም ስህተት አለበት በሚል የቀረበውን ክርክር መርምሮ የይግባኝ ሰሚውን ውሳኔ በመሻር ወይም በማጽናት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ባዔው ወይም ለገቢዎች ቢሮው ሊመልሰው ይችላል።

፫. በክፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠው በ፴ ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

፲፱. የቴምብር ቀረጥ አለመክፈል የሚያስከትለው ውጤት

፩. ማንኛውም ሰነድ በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በሕግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግስት መስሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፤ ምልክት አይደረግበትም ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "1" የተደነገገው በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶችን አይመለከትም፤

፫. በዚህ አዋጅ መሰረት በማስረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከብር 1,000 ማነስ የለበትም ::

፬. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች የተወሰነው ቅጣት ተፈጻሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ከመክሰስ አያግድም፤

፲፫ ከቀረጥ ነፃ ስለመሆን

፩. የክልሉ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የመንግስት መ/ቤቶች ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ናቸው።

፲፬ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚነት

የታክስ አስተዳድር አዋጅ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፲፭ ደንብ እና መመሪያ ስለማውጣት

፩. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ቢሮ ሊያወጣ ይችላል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ገቢዎች ቢሮ ተለይቶ በተሰጡት ጉዳዮች ላይ ለአፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፲፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ የማሻሻያ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ከስመንብረት ዝውውር ጋር ተያይዞ በአንጥልጥል ላይ ያሉ እና የስመንብረት ዝውውር ያልተከናወነባቸው ጉዳዮች በነባሩ አዋጅ የሚስተናገዱ ይሆናል።

፲፯ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎችና አሰራሮች

፩. የቱምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር ፴፩ /፩ሺ፱፻፯፩ ፣ደንቄ/ፎ ሺ ፫፣ ፎደፀ፱/ፎ ሺህ ፱ እና ፎደፀ፭/ፎሺ፲፫ ተሽረዋል።

፪. በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ ተፈጻሚነት አይኖረውም

፲፰. አዋጁ ስለሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ከ_____ ቀን ፎሺ፲፰ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ታህሳስ 17/2018 ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት

የቴምብር ቀረጥ ታሪፍ ሰንጠረዥ

በሰነዶች ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚወሰነው፣ የሚጠየቀውና የሚሰበሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው፡፡

ተ/ቁ	የሰነዱ ዓይነት	የተወሰደ ስሌት መሠረት	የማስከፈያ ልክ	
			ነባሩ	የተሻሻለው
1	የማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም ከታች በተራ ቁጥር 2 ከተመለከቱት ውጭ የሆነ ማናቸውም ሌላ ማህበር የተመሰረተበት መተዳደሪያ ደንብ፣			
	ሀ. መጀመሪያ ሲመዘገብ	በቁርጥ	ብር 350.00	ብር 2,900.00
	ለ. ለስታርታፕ	በቁርጥ	----	ብር 1,000.00
	ሐ. ሲሻሻል	በቁርጥ	ብር 100.00	ብር 700.00
2	የጎበረት ሥራ ማኅበር ወይም የብዙሃን ማህበራት ወይም የሙያ ማኅበራት መተዳደሪያ ደንብ፣			
	ሀ. መጀመሪያ ሲመዘገብ	በቁርጥ	ብር 35.00	ብር 1,500.00
	ለ. ሲሻሻል	በቁርጥ	ብር 10.00	ብር 500.00
3	ግልግል	በዋጋው	የሚተመን 1% የማይታመን ብር 35	የሚተመን 1% የማይተመን ብር 500
4	ማኅቻ(ቦንድ) ወይም የጨረታ ማስከበሪያ ሰነድ	በዋጋው	1%	1%

ተ/ቁ	የሰነዱ ዓይነት	የተወሰደ ስሌት መሠረት	የማስከፈያ ልክ	
			ነባሩ	የተሻሻለው
5	የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሠነድ	በዋጋው	1%	1%
6	ውሎች፣ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው	በቁርጥ	ብር 5.00	ብር 1,000.00
7	የመያዣ ሠነድ			
	ሀ. በብሄራዊ ባንክ ዕውቅና የተሰጣቸው	በዋጋው	-	
	ለ. በፊደል "ሀ" ከተጠቀሰው ውጭ	በዋጋው	2%	2%
8	የሕብረት ስምምነት			
	ሀ. ሊመዘገብ	በቁርጥ	ብር 350.00	ብር 2,900.00
	ለ. ሊሻሻል	በቁርጥ	ብር 100.00	ብር 700.00
9	የቅጥር ውል ስምምነት	የአንድ ወር ደመወዝ	1%	1%
10	ኪራይ የተከራይ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፊያ ሰነድ	በዋጋው	1%	1%
11	ማረጋገጫ	በቁርጥ	ብር 5.00	ብር 100.00

ተ/ቁ	የስነዱ ዓይነት	የተወሰደ ስሌት መሠረት	የማስከፈያ ልክ	
			ነባሩ	የተሻሻለው
12	የውክልና ሥልጣን 1.ውክልና ሲሰጥ ሀ. ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ለሆኑ ለ. ሌሎች ውክልናዎች 2. ውክልና ሲሻር ሀ. ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ለሆኑ	በቁርጥ በቁርጥ በቁርጥ በቁርጥ	ብር 35	ብር 3,000.00 ብር 100.00 ብር 700.00
13	የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ (በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ) ሀ. በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሚወርሱ ወራሾች፣	በዋጋው	1% -	1%
	ለ. ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወራሾች በሞግዚት ሲተዳደሩ ቆይተው የድርሻቸውን ንብረት ሲከፋፈሉ ከዚህ በፊት ለስመንብረት ዝውውር የከፈሉበት ማስረጃ ከቀረበ፣	በዋጋው	ነፃ	ነፃ
	ሐ. የአካል ጉዳተኛ ዜጎች ፣	በዋጋው	2%	1%

ተ/ቁ	የሰነዱ ዓይነት	የተወሰደ ስሌት መሠረት	የማስከፈያ ልክ	
			ነባሩ	የተሻሻለው
	መ. በሞት ወይም በፍች ምክንያቶች የሁለቱ ተጋቢዎች የጋራ ሃብት የሆነ ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት			
	1. አንደኛው ተጋቢ የሌላኛውን ተጋቢ ድርሻ <u>የሚጠቀልል</u> በግማሹ ዋጋ ላይ፣	በዋጋው	-	2%
	2. ሁለቱም ተጋቢዎች ሃብቱን <u>እኩል ከተከፋፈሉ</u>፣	በዋጋው	2%	ነፃ
	ሠ. ከላይ ከፊደል "ሀ" እስከ "መ" ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጭ በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ሲተላለፍ፣	በዋጋው	2%	2%